# ለዕንቁው ኢትዮጵያዊ ዶክተር ጌታቸው ረዳ ዘብሔረ አክሱም

ከሁሉ በተቀዳሚ የተከበረ ስለምታችንን እያቀረብን ከነመላ ቤተሰብዎ ለብርሃነ ልደቱ በሰላም በደስታ አደረሰዎት እንላለን።
በመቀጠልም ዛሬ ሰው ጥፍቶ አገራችን በባንዶችና ቅጥረኞች ተዋናይነት በታሪካዊ ጠላቶቻችን አቀነባባሪነትና ድጋፍ በጥፉት ዋዜማ ላይ በምትገኝበት ወቅት እርስዎና ሌሌው ሰም ጥሩው ኢትዮጵያዊ የትግራይ ተወላጅ ክቡር አቶ ገብረ መድኅን አርአያ ዘወትር ያለማሰልስ ለደረጋችሁትን ለምታደርጉት ወደርየለሽ ተጋድሎ ከፍተኛ ምስጋናችንን እናቀርባለን። በርቱ በርቱ!!
ሰሞኑን አንዳንድ እራሳቸውን ኢሕአፓ ባይ አወናባጆች ሁሉ ከተወሸቁበት ጠባብ ጉረኖ ብቅ እያሉ ሐቁ ሲነገርና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸሙት ሴራቸው በተጨባጭ ማስረጃ ሲጋለጥ ልክ እንደ እብድ ውሻ ያቅነዘንዛቸዋል። እነዚህ ሕሊናቢስ ጉዶች በራሳቸው ስምና ማንነት በሠለጠነ መንገድ በአደባባይ ወጥተው የሃሳብ ክርክር ማድረግ የማይችሉት በጣም ዝቅተኛ ፍጥረቶች፤ በመሳደብና ውሸትን ቆርጦ በመቀጥል ሌላውን ዝም ለማሰኘት የሚያደርጉት ከንቱ ድርጊታቸው ከሽፎባቸል።

በመጀመሪያ ደረጃ በ1966 ዓ.ም የካቲት ወር የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ አመጽ ዓላማና ግብ አዘቅት ያወረደው ወታደራዊ ደርግ ብቻም ሳይሆን ሕዝባዊ ማርክስ ሌኒናውያን ግራ ተራማጅ ብለው ራሳቸውን የሰየሙት ኢሕአፓና መኢሶን ናቸው። ሁለቱ አስመሳይ ማርክሳውያን በፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ በፀረ ፊውዳሊዚም ካባ የኢትዮጵያን ማኅበረሰብ በጎሣና በመደብ ከፋፍለው በማቃረን ሥልጣን በአቋራጭ ለመያዝ ሲበዛ ቋምጠው ነበር። ወታደራዊ ደርግ በታህሣሥ ወር 1967 ዓ.ም መመሪያዬ ሕብረተ ሰባዊነት (Ethiopian Socialism) ብሎ ሲያውጅ ሲቪል ማርክስ-ሌኒናውያን ተራማጅ ነን ባይ የነበሩት መኢሶንና ኢሕአፓ "ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም" ከልሆነ በስተቀር ፀሐይ አትጠልቅም እያሉ በሾሻሊዝም ካባ እስታሊናዊ አረመኔ ፀረ ዴሞክራሲ ሥርዓት በኢትዮጵያ ለማስፈን ነበር የተንቀሳቀሱት። መኢሶን ከደርግ ጋራ ወግኖ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ሊመሠርት፣ ኢሕአፓ ደግሞ ደርግን ፋሽስት ብሎ በመሰየም ከሁለቱ ተባባሪዎች በተጻራሪው አሁኑኑ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት በነሱ ኮሚኒስት ፓርቲ ግንባር ቀደም መሪነትና ተባባሪ ጀሌዎች ካልተመሠረተ ብለው የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ የሚቃረን ዘመቻቸውን አፋፋሙት። በየካቲት ወር 1967 ዓ.ም ደርግና መኢሶን የመሬት አዋጅ አውጥተው የኢትዮጵያን ገበሬ በመላው አገር የመንግሥት ጭሰኛ የሆነበትን ሥርዓት በገጠር ዘርግተዋል። በመቀጠልም በሐምሌ ወር ደግሞ የከተማ ቦታ ትርፍ ቤት አዋጅ አውጥተው የጭቃ ቤትና ትንንሽ ጎጆዎች ሳይቀሩ ተወርሰው

የከተማ ነዋሪዎችን ለከፋ የቤት እጦት ችግር ተዳርገዋል። በመኢሶንና ኢሕአፓ መካከል የነበረው የቃላት እንካሲላንታ ፀረ አብዮተኛ፣ ንዑስ ከበርቴ፣ ከሃዲ ወዘተረፈ ወደ መገዳደል ተቀይሮ የመኢሶን አባል የነበረውን ዶክተር ፍቅሬ መርድን በመስከረም ወር 1968 ዓም ሲገደል፣ በቀጣዩ ደግሞ በጥቅምት ወር ጌትነት ዘውዱ የሠራተኛና ማኅበራዊ ሚኒስትር ፅሐፊ በኢሕአፓ ነፍሰ ገዳይ ቡድን ተገድሏል። በተከታታይ የመኢሶን ደጋፊ የነበሩ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች ጋዜጠኞች፤ ሠራተኞች፤ ወዘተረፈ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በገፍ ተጨፍጭፈዋል። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተቋቋሙት 247 የቀበሌ ማኅበራት ውስጥ 148 የሚሆኑት ለቂ መንበሮች የኢሕአፓ ግድያ ሰለባ ሆነዋል። ስለዚህም ነው ከመጋቢት ወር እስከ ሚያዚያ ወር ማለቂያ መኢሶንና ደርግ የቀበሌ አብዮት ጥበቃ አባላትንና የአዲስ አበባ ዙሪያ ገበሬ ማኅበራት ታጣቂዎችን አሰማርተው ከፍተኛ አሰሳ ተደርጎ ኢሕአፓ ከአዲስ አበባ የተመነጠረው። የኢሕአፓ መሪ ተብዬ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይና አስገዳይ ሁሉ በኢትዮጵያውያን ክቡር ደም ማፍሰስ የተሳከሩት አረመኔዎች፣ ከሰውነት ወደ አውሬነት ደረጃ የተለወጡት በዚያን ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤ የመንግሥት ተቋማት መሥሪያ ቤት ሕንፃዎች ግርግዳ ላይ ፣

እናንተም ግደሉ እኛም እንገድላለን፣
እናንት ግን ትቢያ እኛ እንነሳለን።...........................

እያሉ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ እንደሆኑ አስመሰለው፤ ሕፃናትን በከተማ ፋኖ ነፍሰ ገዳይነይት አስማርተው የነበሩት የኢሕአፓ መሪ ተብዬዎች አብዛኛዎች በደርግና መኢሶን ትብብር ትቢያ ሆነዋል። ሆኖም ግን ጥቂት የመኢሶንና ኢሕአፓ መሪዎችና ጀሌዎች አምልጠው በአውሮፓና አሜሪካ የሚገኙት ተገቢ ፍርዳቸውን ሳያገኙ ማርጀታቸውና ለሞት መቃረባቸው እጅግ በጣም ያሳዝናል።

እነዚህ ሁለቱ ድርጅቶች ቀደም ብለው ከየካቲት ሕዝባዊ አመጽ በፊት በአውሮፓና አሜሪካ ጎራ ለይተው ርስ በርስ ሲነታረኩ የነበሩት ናቸው ግስግሰው አገር ቤት በመግባት ኢትዮጵያን አዘቅት ያወርዷት። የሁለቱ ድርጅቶች ለሥልጣን መያዝ ባደረጉት ግብግብ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ ለማይታወቅ ለነጭና ቀይሽብር መቀሰፍት፤ ለአገር አጥፊውና ጠፊው ወታደራዊ ደርግ መንሰራፋት እንዲሁም ለተከታዩ የፀረ ኢትዮጵያ ቅጥረኛው ወያኔ ትግሬ የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዳረጉ መቼም አሌ አይባልም።

ኢሕአፓ በተለይ አንድም የገጠር ብዙኃን ሕዝብን ድጋፍ ሳይኖረው በተማሪዎችና አስተማሪዎች እንዲሁም ጥቂት ከተሜ ንዑሥ ከበርቴዎችን በመያዝ በከተማ ፋኖነት ደርግን ደምስሶ ሥልጣንን ለመያዝ በከፈተው ጦርነት ነው ድባቅ የተመታው። በድርጅቱም ውስጥ በተፈጠረው አንጃ ምክንያት ተመንጥሮ ወድሟል።

እነክፍሉ ታደሰ ያዲስ አበባን ተማሪና አስተማሪ፣ ሠራተኛ አስፈጅተው ከአዲስ አበባ ወደሰሜን ትግሬ የፈረጠጡት በወያኔ ሕወሐት ድባቅ ተመተው ከአሲምባ ሲባረሩ ወደ ጎንደር ሸሽተዋል። ጎንደር የገቡትም ከአራት ተከፍለው የጎንደርን ገበሬ ቁም ስቅል ማሳየት በመጀመራቸውና የደርግ ወታደር አካባቢውን በማጽዳት አባሯቸዋል። ጥቂቶች ወደ ወያኔ ሕወሓት እጅ ሰጥተው ተቀላቅለዋል። ከጎንደርም ወደ ሱዳን ሽቃጣቸውን ጠቅልለው ትግል በቃን ብለው ገብተዋል። ከሱዳንም በአብዛኛው ወደ ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ በስደተኛነት ተወስደዋል።

ኢሕአፓ እንደ ወያኔ ሕወሓት ድል ቢቀናው ኖሮ በዚያን ጊዜ ከወያኔ ሕወሓት የተለየ ምንም ነገር ማድረግ አይችልም ነበር። እንዲያውም ሐቀኛ ያውሮፓ፤ ያሜሪካና አፍሪቃ ሀገራት የፖለቲካ ሁኔታ ተንታኞች በግልጽ እንዳሰፈሩት ጽንፈኛው ኢሕአፓ በደርግና መኢሶን ባይሸነፍ ኖሮ ኢትዮጵያን ልክ እንደ ካምቦዲያው ፖልፖት ያደርጋት ነበር።

ኢሕአፓና መኢሶን የኤርትራን የመገንጠል እንቅስቃሴ በይፋ ደግፈዋል። ለኡጋዴን ነዋሪ ሱማሌዎችም ቢፈልጉ ተገንጥለው ከታላቋ ሱማሌ ሪፑብሊክ ጋራ እንዲዋሃዱ ተስማምተዋል።

ዛሬ ደግሞ ጥቂት በጡረታ ላይ በሕይወት ያሉት የቀድሞ አባላት ነፍሰ ገዳይና አስገዳዩች እንደ ክፍሉ ታደስ፣ ኢያሱ ዓለማየሁ፣ መርሻ ዩሴፍ፣ ፋሲካ ወዘተረፈ የመሳሰሉት ዓይናቸውን በጨው አጥበው ከሻዕቢያ፣ ከሰይድ ባሬ፣ ከግብፅ ወዘተረፈ ጋራ ምንም ግንኙነት አልነበረንም፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ልዕላዊነት ከጧቱ ጀምሮ የቆምን ነበርን እያሉ ሲያናፉ መስማት እጅግ በጣም ያሳምማል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወንጀለኛው ክፍሉ ታደስ የነጭ ሽብር አዝማች ጌታቸው ማሩን አስገድሎ እሬሳውን እንኳ ያበላሸ አረመኔ በሆላንድ ፍርድ ቤት በደርግ መንግሥት አባል ወንጀለኛ ላይ ምስክር ሆኖ መቅረቡን ስንሰማና ሌሎችም የኢሕአፓ ወንጀለኞች በመላው በተለይም መሪ ተብዬዎቹ እንደ ኢያሱ ዓለማየሁ ወዘተረፈ ያሉት ለፍርድ ሳይቀርቡ በአውሮፓና አሜሪካ ከተሞች እየኖሩ ሳይሞቱ በፊት ለፈጸሙት ወንጅል ተገቢውን ፍርድ አለማግኘታቸው በጣም አሳሳቢ ነው።

የፀረ ኢትዮጵያ ናዚው ባሮን የሮማን ፕሮቻዝካና ተከታዩቹ የአፍሪቃ ቅጥረኛ አማጽያን የጎሣ ነፃ አውጭዎች የነሻዕቢያ፣ የሕወሓት፣ የኦነግ፣ የምዕራብ የሶማሌ ወዘተረፈ የመስክ አማካሪዎችና የጎሣ ጥናት የፈጠራ ድርሰት አዘጋጆችና የፀረ ኢትዮጵያ ጥላቻና ቅስቀሳ ዋና አስተባባሪ የሆኑት የእንግሊዝና የግሪኩ መጢቃ ጆን ማርካኪስ፤ የአንግሊዞቹ ግሪንፊልድና ባስ ዳቪሰን ወዘተረፈ ምልምል የነብረው ባንዳ ወሎዬ የጀብሃ አሽከር ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያን አገርነት፣ ልዑላዊነትና ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛነትን ውሸት ነው እያለ ልክ የፋሽስት ጣሊያን ወራሪዎችን ፕሮፓጋንዳ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲት ተማሪዎች ማኅበርን መድረክ በማድረግ ሲነዛ የነበረ የዱቼ ሙሶሎኒ ግልገል ጥቁር ሸሚዝ ፋሽስትን ኢሕአፓ ተብዬዎች ልዩ ክቡር አይነኬ ነገር አድርገውት የዚህን ወራዳ ከሃዲ ድርጊት ለመሸፈን ሲያሽቃብጡ ትንሽ እንኳ ዕፍረት የላቸውም።

በመጨረሻም የኢሕአፓ ተብዬ ሙት ድርጅት መሪና አባል ነን ባይ ጥርቅምቃሞ ደናቁርት ሁሉ በተከበሩት የኢትዮጵያ ሰማይ ድረ ገፅ አዘጋጅና መጻሕፍት ደራሲ ዶክተር ጌታቸው ረዳ ላይ በእውነትና ሐቅ ጥላቻ ፍጽም ዓይናችሁ ታውሮ የምትነዙትን ትርኪ ምርኪና የባለጌ ስድብ ዘመቻችሁን በአስቸኳይ አቁሙ! ይህን ቦርቃቃና ሞጥሚጣ አፋችሁን ዝጉት። ከጌታቸው ረዳ ላይ እጃችሁን አንሱ! ዳሩ ግን አላርፍ ብላችሁ በመወሻከታችሁ ብትቀጥሉበት ኢሕአፓ ይባል የነበረውን የጠራቢ ድርጅት ምንነት በሰፊ ማስረጃዎቻችን ከሥር መሠረቱ ለማጋለጥ በማንኛው ጊዜና ስፍራ ተዘጋጅተናል። ጆሮ ያለው ይስማ!!!!!!

እነ ገሞራው ማንያዘዋል፣ የውብዳር ዘለቀ፣ ገብሬ ጉልቱ፣ ገለበው ሰንጎጎ ተከስተ ሃጎስ፣ ዘውዴ በዳዳ፤ አዩ ይስማን፣ ኃይለ ልዑል ይርጋ

ከኢትዮጵያውያን ማኅበር ጥናትና ምርምር ዘርፍ

tomy.gemora16@gmail.com